# ዴሞክራሲያ

" የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን"

ቅፅ 49፣ ቁ. 1 ሰኔ 2013 ዓ. ም


## የአገራችንን ሕልውና ለማረጋገጥ በአንድነት እንቁም!

አገራችን ኢትዮጵያ አሁን የገጠማት ችግር መጠንና ጥልቀቱ ብሔራዊ ክብሯንና ሕልውናዋን የሚፈታተን ሆኗል። ኢሕአፓ የውስጥና የውጭ ችግሮችን በዝርዝር ከተመለከተ በኋላ ዘርፈ-ብዙውን ችግር ለመቋቋም ከመንግሥት፣ ከፖለቲካ ድርጅቶችና ከሕዝብ የሚጠበቁትን የመፍትሄ አቅጣጫዎች ማመላከት አስፈላጊ ሆኖ አግኝቶታል።

በአገራችን ውስጥ ጎልተው የሚታዩት ችግሮች ዛሬ ላይ ከሚገኙበት እጅግ አሳሳቢ ደረጃ ከመድረሳቸው በፊት "ለውጡ የት ገባ?" በሚል ርዕስ በ2011 ዓ. ም በልሳናችን በዴሞክራሲያ ቅፅ 47 ቁጥር 2 ላይ የሚከተሉትን ምክረ-ሃሳቦች አቅርበን ነበር።

- የለውጡ ተቃዋሚዎች ሕዝብ በሰላም እንዳይኖር ሲያደርጉ እንዲሁም አክራሪ ብሔርተኞች ሕግ ሲጥሱ መለማመጥ ሳይሆን ሕጋዊ እርምጃዎች እንዲወሰዱ፣
- የችግር ምንጭ የሆነውን ሕገ-መንግሥት በብሄራዊ ዕርቅ መንፈስ ለውይይት ማብቃትና በውሳኔ-ሕዝብ ማፀደቅ፣ የክልል ጥያቄ የሚያነሱትን ዞኖች ካሉ ጥያቄያቸው በይደር እንዲቆይ፣
- ስድስተኛው ሀገራዊ ምርጫ ሰላምና መረጋጋት ከማምጣት ይልቅ፣ ያሉትን ችግሮች እንዳያባብስና ለአክራሪዎች አቅም እንዳይሰጥ እንዲዘገይ የሚሉ ነበሩ።

ምክረ-ሃሳባችን ተግባራዊ ባለመደረጉ በሕዝብ ከፍተኛ መስዋዕትነት የመጣው ለውጥ በውስጥ ችግሮች ተተብትቦና የውጭ ጫናዎችም ታክለውበት አገራችን አሁን የምትገኝበት ደረጃ ላይ ደርሳለች።

የውስጥ ችግሮቻችን በአብዛኛው ምንጫቸው ዘርና ቋንቋ ተኮር ተደርጎ የተዋቀረው ፌደራላዊ አስተዳደሩና ለዚህም ዋና መሠረት የሆነው ሕገ-መንግሥቱ ነው። ዘረኝነትን የሚያጎላ፣ የሕዝቡን ታሪካዊ ትስስር ከግምት ውስጥ ያላስገባ፣ "እኛና እነሱ" ብሎ በመለያየትና አዳዲስ ቅራኔዎችን በመፍጠር የእኔ ብቻ ባይነት ሥነልቦና እንዲጎለብትና ፀረ-አንድነት አመለካከት ገዝፎ እንዲገኝ የሚያበረታታ ሕገ-መንግሥት ነው በሥራ ላይ ያለው። በመሆኑም በገጠርም ሆነ በከተማ ዜጎች በሰላም ከቤታቸው ወጥተው መመለሳቸው ብርቅ እየሆነ የመጣበት ጊዜ ላይ ትገኛለች ሀገራችን። በአንዳንድ ክልሎች ዜጎች በጠራራ ፀሐይ ታፍነው እየተወሰዱ የት እንደደረሱ አይታወቅም። በየቀኑ የሚታየውና የሚሰማው ከማንነት ጋር የተያያዘ መፈናቀልና ግድያ ነው። በማንነት ላይ የተመረኮዘውን እኩይ አስተሳሰብ የህወሓት አገዛዝ ባዋቀረው አስተዳደሩ አማካኝነት ከሠላሳ ዓመታት በላይ በሥራ እንዲተገበር አድርጓል። ይህም በመሆኑ ህወሓት ዛሬ ከማዕከላዊ መንግሥት ሥልጣኑ የተወገደ ቢሆንም ያዋቀረው ህገ-መንግሥት፣ የክልል አወቃቀርና ትርክት ግጭትን፣ የእርስ በእርስ አለመተማመንንና አንዱ የሌላው የበላይ ሆኖ ለመቀጠል የሚደረግ ትንቅንቅ እንዲቀጥል እያደረገ ነው። በገዥው ፓርቲ በብልጽግና ውስጥ እየታዬ ያለው፣

ለምሳሌ በአማራ ክልላዊ መንግሥት ብልጽግናና በኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ብልጽግና መካከል የሚደረገው ትከሻ ለትከሻ መለካካት ብዙ የሕይወት ዋጋ እያስከፈለ ነው።

በተለያዩ የሃላፊነት ቦታዎች ላይ ያሉት አፍቃሪ ህውሓት ኃይላት አድብተው ህወሓት እንደገና እንዲያንሠራራ ለማድረግ እየጣሩ ነው። ይህም ሕዝብ እርስ በርሱ እንዲጋጭና ውስጣዊ ሰላሙ እንዲደፈርስ በማድረግ፣ ከዛም ባለፈ ከፀረ-ኢትዮጵያ ኃይሎች ጋር በማበር አገሪቱን ለውጭ ጠላት አጋልጦ በመስጠት አስጊ ሁኔታ እንዲፈጠር አድርገዋል።

የህወሓት የዘረኝነት መርዝ ፍሬ አፍርቶ ሕዝብን እርስ በእርስ ከማፋጀት አልፎ አገራችንን ወደ ይፋዊ ጦርነት ውስጥም አስገብቷታል። ኢትዮጵያውያን ተወልደው ባደጉበት፣ አያት ቅድመ አያቶቻቸው ለአገር ዋጋ ከፍለው ዘር ተክተው ባለፉበት አገር፣ ልጅና የልጅ ልጆቻቸው እንደ መጤ ተቆጥረው ደማችሁ ከእኛ አይመሳሰልም፣ ከክልላችን ውጡ እየተባሉ በጠራራ ፀሐይ በአሰቃቂ ሁኔታ እየተገደሉ፣ ከቀያቸው እየተፈናቀሉ፣ ሀብት ንብረታቸው የሚቃጠልባት አገር ውስጥ እየኖሩ ነው። ይህ ጥቃት በአብዛኛው በአማራ ማኅበረሰብ አባላት ላይ ያተኮረ ሲሆን በመላው የሀገሪቱ ክፍሎች ውስጥ የሚኖሩ የሌሎች ማኅበረሰቦች አባላትም የዚሁ ግፍ ሰለባ ሆነዋል።

“ሰው የሚያጭደው የዘራውን ነው” እንደሚባለው መንግሥት ተፎካካሪ ፓርቲዎችን ከውጭ ወደ አገር እንዲገቡ ሲጋብዝ አንዳንድ ድርጅቶች ግልጽ ባልሆነ መንገድ ከነትጥቃቸው እንዲገቡ መፍቀዱ፣ የነበረውን የዘረኝነት መርዝ ይበልጥ እንዲስፋፋ አድርጎታል። አሁን በኦሮሚያና አጎራባች ክልሎች እየተደረገ ላለው ግድያና መፈናቀል ከፍተኛ ሚና እየተጫወተ ያለው በቅርቡ በዘረኝነት የተፈረጀው የኦነግ ሸኔ አሸባሪ ቡድን ነው። የዘረኝነት ነዳጅ እያርከፈከፉ ሕዝብ ሲያስፈጁና ታጣቂ የጥፋት ኃይሉን የልብ ልብ ሲሰጡት በነበሩ ግለሰቦች ላይ ሕዝብ እርምጃ እንዲወሰድባቸው በሚጠይቅበት ወቅት መንግሥት የዝሆን ጆሮ ይስጠኝ አለ። አንዳንዶችም በአደባባይ “ማን ትጥቅ ፈቺ ማን ትጥቅ አስፈቺ ሊሆን ነው” ይሉ ስለነበረ ይህ አባባል እነሆ አሁን ለደረስንበት መራር የሆነ ሬሳ ቆጠራ ውስጥ እንድንገባ የራሱን ሚና ተጫውቷል።

ህወሓት ከመንግሥት እኩል ሊገዳደር የሚችል ልዩ ጦርና የሚሊሺያ ኃይል እያሠለጠነና “ትግራይ የጠላቶቻችን መቃብር ትሆናለች” እያለ በአደባባይ ሲፎክር፣ እንዲሁም የሀገር መከላከያ ኃይልን ለመምታት እቅድ ሲያወጣ የደህንነት ክፍሉ እንዴት መረጃ ማግኘት ተሳነው?

ከሰላም ዕጦት በተጨማሪ የአገራችን ኤኮኖሚ የተናጋ በመሆኑ ሕዝቡ በየቀኑ እየተጋፈጠው ያለ ሃቅ ነው። ገቢው ሊያድግ ያልቻለው የግል ንግድ ተቋም፣ የመንግሥት ሠራተኛ፣ በዝቅተኛ ንግድ ላይ የተሰማራው ነጋዴ፣ ገበሬው፣ ወጣቱ፣ እናቶችና አዛውንቱ የዋጋ ግሽበቱና የኑሮ ውድነቱ ከአቅማቸው በላይ ሆኗል። የዶላር ምንዛሬ በማሻቀቡና የብር የመግዛት አቅም እያሽቆለቆለ በመሄዱ አስመጭና ላኪ ነጋዴዎች ዕለታዊ የንግድ እንቅስቃሴያቸውን ማካሄድ የማይችሉበት ደረጃ ላይ እየደረሱ ነው። አገር ውስጥ በሚገቡ ዕቃዎች ላይ በመንግሥት የተጣለው ቀረጥ ዕቃው ከተገዛበት ዋጋ እጥፍ እየሆነባቸው ቀረጥ ከፍለው ዕቃቸውን ለማውጣት የሚቸገሩ አነስተኛ ነጋዴዎች ቁጥር ቀላል አይደለም። የአገር ውስጥ የምርት ዋጋም የትዬለሌ ነው።

ከዚህ በተጨማሪ የዕለት ተዕለት ጉዳዮችን ለማስፈጸም የመንግሥት ባለሥልጣናት አይደረሴነት ሕዝቡን እያማረረው ነው። ባለጉዳይ አንድ መሥሪያ ቤት ሲሄድ የሚሰጠው መልስ ባለሥልጣኑ “ወጥተዋል፣ ስብሰባ ላይ ናቸው. . .ወዘተ” የሚል ነው። በአጭሩ በብዙ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ውስጥ የሚታየው አሠራር ሕዝብን የማንገላታት፣ በሙስና የተተበተበና ተጠያቂነት የሌለበት ነው።

አገራችን አሁን ላለችበት አስከፊ ሁኔታ ከዳረጓት ምክንያቶች ውስጥ አንዱ የአገር ጉዳይ ይገደናል የሚሉ ተፎካካሪ ፓርቲዎች በጋራ ቁጭ ብለው በሚስማሙባቸው ጉዳዮች ላይ አብረው ለመሥራት አለመቻላቸው መሆኑን ኢሕአፓ በድፍረት ይናገራል። የውስጥ ጠላቶች የፈጠሩትን ችግርና የውጭ ጠላቶች በአገራችን ላይ የሚያደርጉትን ጫና በመቃወሙ ላይ አብዛኛዎች ተፎካካሪ ፓርቲዎች አቋማችን ተመሳሳይ ነው። ሆኖም ግን ሀገራችን በገጠማት ዋና ዋና ጉዳዩች ላይ በአንድነት የሕዝብና የሀገር ድምፅ የመሆን ሃላፊነትን በአግባቡ የመወጣት ሥራ ጎልቶ ሊወጣ አልቻለም። ኢሕአፓ እንደትላንቱ ዛሬም ሀገራችንና ሕዝባችን ከተደቀነባቸው አደጋ ለመታደግ የፖለቲካ ድርጅቶች አስቸኳይ ምክክር በማድረግ አገር አድን የተግባር መመሪያ ማውጣት አለብን ይላል።

በጥቂት ቀናት ውስጥ ስድስተኛው ሀገራዊ ምርጫ ይካሄዳል። ኢሕአፓ በረጅም ታሪኩ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ራዕዩን በሕጋዊ መንገድ ለሕዝብ ይፋ በማደረግ 103 ዕጩዎችን በተፎካካሪነት አቅርቧል። ሀገራችን ያለችበትን የፖለቲካ ድባብ ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ምርጫው ለኢትዮጵያዊ የአንድነት ኃይሎች በህጋዊው የፖለቲካ መድረክ ላይ ትርጉም ያለው ሚና ለመጫወት ዕድል ይከፍትላቸዋል ብሎ በማመን ነው ኢሕአፓ ምርጫው መካሄዱን የሚደግፈው። በዚህ አኳያ ከምርጫው በፊት፣ በምርጫው ወቅትም ሆነ ከምርጫው በኋላ ሂደቱ በሰላም እንዲጠናቀቅ ኢሕአፓ የበኩሉን ያደርጋል።

ሀገራዊ ምርጫው በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምክንያት የተራዘመ መሆኑ ይታወቃል። ዛሬም ሕዝባችን በበሽታው እጅግ እየተጠቃ መሆኑ በጣም አሳሳቢና ኣሳዛኝ ነው። በዚህ አኳያ መንግሥት የጥንቃቄ ትምህርቶችንና የምርመራ ተደራሽነትን በማስፋፋት፣ እንዲሁም የህክምናና ሌሎች ድጋፎችን ብቃት በማሳደግ ሃላፊነቱን ይበለጥ አጠናክሮ ሊቀጥል ይገባዋል እንላለን። በተጨማሪ፣ የወረርሽኙ ጉዳዩ ለመንግሥት ብቻ የሚተው ሳይሆን ዜጎችና የተለያዩ ተቋማት የወገኖቻችንን ሕይወት ለመታደግ ያላሰለስ ጥረታቸውን አጠናክረው እንዲቀጥሉ ማድረግ ይገባል፣ ኢሕአፓም የድርሻውን ይወጣል።

መንግሥት ከአሸባሪው ህወሓት ጋር ባደረገው ጦርነት ምክንያት ለችግር የተጋለጠውን የትግራይ ሕዝብ ለመርዳት እያደረገ ያለውን ጥረት አጠናክሮ መቀጠል አለበት እንላለን። ዕርዳታው እንዳይደርስ ከሕዝብ ጋር ተመሳስለው ወንጀል የሚፈጽሙ፣ የዕርዳታ ሰጭ ሠራተኞችን በሚገድሉ የህወሓት ቅሪቶች ላይ የተጠናከረ እርምጃ በመውሰድ ሕግና ሥርዓትን ማስከበር እጅግ አስፈላጊ መሆኑን አጠንክረን ለመግለጽ እንወዳለን።

ከውስጣዊ ችግሮቻችን በተጨማሪ ለሀገራችን በጎ ተመኝተው የማያወቁ እንደ ግብፅ ዓይነቶቹ መንግሥታት በተፈጥሮና በታሪክ ከአገራችን ጋር የተሳሰሩትን ቀይ ባህርና የአባይን ወንዝ ለሰላሟ ጠንቅ እንዲሆኑና ሉዓላዊነታችንን ለማናጋት ተግተው እንደሚሠሩ ደጋግመን አይተናል።

በታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ምክንያት ከግብፅና ከሱዳን ጋር የተፈጠረው አለመግባባት ለሦስቱ አገሮች ብቻ ሳይሆን ለአፍሪቃ ቀንድ ሀገራትም ከፍተኛ ስጋት እየሆነ መጥቷል። በተለይም በህወሓት ተጠንስሶ፣ በሌሎች አክራሪ ብሔርተኞች ተባባሪነት በሀገራችን ውስጥ እያደገ የመጣውን ማንነትን መሠረት ያደረገ ግጭትን ተጠቅመው ሱዳንና ግብፅ "ጊዜው አሁን ነው" በሚል ስሌት በሀገራችን ውስጥ ከፍተኛ ችግር ከመፍጠራቸውም በላይ የበለጠ ሊያባብሷቸው እንደሚችሉም መረዳት ይገባል።

አባይን አስመልክቶ ከዓመታት በፊት የተፋሰሱ አገሮች የጀመሩት ንግግር ተቋርጦ ችግሩም ሆነ ድርድሩ በግብፅ፣ ሱዳንና በኢትዮጵያ ብቻ ተወስኖ እልህ አስጨራሽ ውይይት ተካሂዷል። በአገራችን ላይ ያንዣበበው ጥቁር ደመና ከቃላት ጦርነት አልፎ ጦር ሊያማዝዝ የደረሰ ሆኗል። ማዕከላዊ መንግሥት ከህወሓት ጋር ባካሄደው ጦርነት ወቅት አጋጣሚውን ተጠቅማ ሱዳን በግብፅ አደፋፋሪነት የአገራችን ድንበር ጥሳ በመግባትና የጦር ኃይል አስቀምጣ ግድባችንን አሻግራ እየተመለከተች ትገኛለች። የህወሓት ጦርና ሁመራ አካባቢ ሳምሪ የተባለው ነብሰ ገዳይ ቡድን ማይካድራ ላይ ሰላማዊ ሰዎችን በአሰቃቂ

ሁኔታ ጨፍጭፎ ወደ ሱዳን ሸሽቷል። የሳምሪ ቡድን በሱዳን ተባባሪነት እንደገና ተደራጅቶ ኢትዮጵያን ለመውጋት በምዕራቡ የአገራችን ክፍል በተደጋጋሚ የሞከረ ቢሆንም በመከላከያ ኃይላችንና የአማራ ሚሊሺያ በተደጋጋሚ ተመትቷል።

የኢትዮጵያን መንግሥት በጦር አንበርክኮ አሸባሪውን ህወሓት ወደ ሥልጣን ለመመለስ እንዲቻል ሱዳንና ግብፅ ለአሸባሪ ኃይሎች ድጋፍና ትብብር እያደረጉ ነው። ግብፅ ሱዳን ውስጥ የጦር ካምፕ እየመሠረተች እንደሆነ ሱዳን ትሪብዩን (የሱዳን ጋዜጣ) አስነብቧል። በቅርብ ደግሞ ኬንያና ግብፅ ወታደራዊ ስምምነት መፈራረማቸውንም ሰምተናል። ጅቡቲ ውስጥ ያለው የአሜሪካ ወታደራዊ ተቋም ለግብፅ ወታደራዊ ኃይል ቦታ ሰጥቶ ግብፅ ጦር ያሠፈረችው ከዓመታት በፊት ነው። አሁን ደግሞ ግብፅ ጅቡቲን ከጎን ለማሰልፍ የምታደርገውን ጥረት እየተመለከትን ነው።

አሜሪካ ቀደም ሲል በአባይ ጉዳይ ሦስቱ አገሮች በሚያደርጉት ድርድር ላይ አደራዳሪ ሆና ለመቅረብ በኢትዮጵያ ላይ እጅ የመጠምዘዝ ሙከራ ብታደርግም ኢትዮጵያ የማትቀበለው መሆኑን በማያሻማ መንገድ ግልፅ አድርጋለች። ስለዚህም አሜሪካ ከጀርባ ሆና ድርድሩ የሁሉንም ወገኖች ጥቅሞች በሚያስከብር መልኩ ሳይሆን የግብፅን ፍላጎት በሚያሟላ መልኩ ብቻ እንዲጠናቀቅ ሰፊ ግፊት እያደረገች ትገኛለች። በዚህ አኳያ የቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዘዳንት ዶናልድ ትራምፕ "ግብፅ ግድቡን ልታፈርሰው ትችላለች" በማለት ተገቢ ያልሆነ ንግግራቸው በመገናኛ ብዙሃን መደመጡን ልብ ይሏል። አዲሱ የጆ ባይደን አስተዳደርም ከግብፅና ከሱዳን ጋር ያለውን ወገንተኝነት በግልፅ እያሳየ ነው። ከአሸባሪው ህወሓት ጋር ትግራይ ውስጥ በተደረገው ጦርነት የሙብት ጥሰት ተፈጽሟል፣ የኢትዮጵያ መንግሥት ሕዝብ እየተራበ በቂ ዕርዳታ እንዳይደርስ አድርጓል በማለት በህወሓት ላይ የሚወሰደው ወታደራዊ እርምጃ እንዲቆምና ህወሓትን ወደ ህጋዊው የፖለቲካ መድረክ ለመመለስ ድርድር እንዲደረግ ከፍተኛ ጫና እያሳደረ ነው። የአማራ ክልል ሚሊሺያና የኤርትራ ጦር ወልቃይት፣ ጠገዴ፣ ፀለምትና ራያን ለቅቆ ይውጣ በማለት የህወሓትን ጥያቄ በአደባባይ ከማስተጋባቱም በላይ በኢትዮጵያና በኤርትራ ባለሥልጣኖች ላይ የቪዛ እገዳ መጣሉንም አስታውቋል።

የትግራይ ሕዝብ ክብሩ ተገፎ ሰብዓዊ ሙብቱ ተደፍሮ፣ በምንም መስፈርት ተቀባይነት በሌለው የረሃብ፣ የጦርነትና የፆታዊ ጥቃት ከቶም ሰለባ ሊሆን አይገባውም። እየተዘገቡ ያሉት ኢ-ሰብዓዊ ድርጊቶች በህወሓት ቆስቋሽነት የተከፈተው የአውዳሚው ጦርነት መዘዝ ውጤቶች ናቸው። ስለሆነም ኢ-ሰብዓዊ ድርጊቶች በአስቸኳይ እንዲቆሙና አስፈላጊው ዕርዳታና ድጋፍ ሁሉ ለትግራይ ሕዝብ እንዲደረስ፣ በፆታ ጥቃትም ሆነ በሙብት ጥሰት የተሳተፉት ሁሉ እየተጣራ በደል ፈጻሚዎች ለፍርድ እንዲቀርቡ መደረግ አለበት።

ከዚህ አኳያ "አሜሪካ እውን በትግራይ ሕዝብ ላይ ደረሰ የተባለው በደል አሳስቧት ነው በአገራችን የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ የገባችው?" ብሎ መጠየቅ ተገቢ ይመስለናል። በኢሕአፓ እምነት አሜሪካ በትግራይ ሕዝብና በሰብዓዊነት ስም እያደረገች ያለችው ጣልቃ ገብነት የአሜሪካን ፍላጎት በኢትዮጵያና በአፍሪቃ ቀንድ ብሎም በአፍሪቃ ያላትን ጥቅም ለማስጠበቅ የምታደርገው ጥረት ከመሆን አያልፍም።

ቻይና በኢትዮጵያም ሆነ በአፍሪቃ ኤኮኖሚ በሰፊው የገባች መሆኑ ግልጽ ነው። በቅርቡ ደግሞ ራሺያ ከኢትዮጵያ ጋር በዩራኒም ማዕድን ቁፋሮ ስምምነት ላይ መድረስ፣ የራሺያ ጦር በሰሜን ሱዳን የቀይ ባህር ጠረፍ ላይ የጦር ሠፈር ግንባታ፣ የቱርክ በፖርት ሱዳን አካባቢ አንድ ደሴት ላይ ጦር ለማስፈር ከሱዳን ጋር ንግግር ማድረግ፣ የኤርትራና የኢትዮጵያ ስምምነትና ከዚያም አልፎ ኢትዮጵያ የአሰብን ወደብ ልትጠቀም መሆኗ፣ የሱማሌ፣ የኢትዮጵያና የኤርትራ መንግሥታት የወዳጅነት ውል መፈራረም፣ አሜሪካ የአፍሪቃ ቀንድ አገሮችን አስተባብረው በጥቅሜ ላይ ይመጣሉ ብላ በመስጋቷ ነው በኢትዮጵያ ላይ ጫና ማድረግ የፈለገችው ብንል ስህተት አይመስለንም። የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት ኢትዮጵያን ሲገልጻት "ኢትዮጲያ ለአፍሪካ ቀንድ ምሰሶ የሆነች ሀገር ነች" "Ethiopia is critical anchor in the horn of Africa"

ብሏል። በኛ እይታ አሜሪካ በአሁኑ ሰዓት በሀገራችን የሰብዓዊ መብት ተሚጋች መስላ ለመታየት መጣሯ ከእራሷ አገርዊ ጥቅም አኳያ እንጂ የኢትዮጵያውያን የሰብዓዊ መብት ጉዳይ አንገብግቧት አይደለም ነው የምንለው። አሜሪካ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሰብዓዊ መብት የምትቆረቆር ቢሆን ኖሮ አሸባሪው ህወሓት ከአርባ ዓመት በላይ የኢትዮጵያን ሕዝብ መከራ ሲያወርድበትና የሰብዓዊ መብት ጥሰት መረን በለቀቀበት ዘመን በስቴት ዲፓርትመንት በዓመት አንድ ጊዜ ከሚወጣ ልፍስፍስ ዘገባ በስተቀር ምንም ተንፍሳ አታውቅም፣ ህወሓት የአሜሪካ ታማኝ አገልጋይ ነበርና። በተጨማሪም አሁን በቅርቡ በማይካድራ በህወሓት ተቀነባብሮ የተፈጸመውን በአማራ ማኅበረሰብ ላይ ያተኮረ ጭፍጨፋ አሜሪካም ሆነች አጋሮቿ ድምፃቸውን አላሰሙም፣ የወንጀል ፈጻሚው ህወሓት መሪዎች በሕግ ይጠየቁ ሲሉ አልተደመጡም።

ከላይ ያቀረብናቸው የኢትዮጵያ ሕዝብ በሚገባ የሚያውቀውን እውነታ ለማንሳት የተገደድነው፣ በአገራችን ላይ ከፍተኛ አደጋ እያንዣበበ እንደሆነ እንዲጤንና አገራችንን ከዚህ አደጋ ለማዳን ቅድሚያ ለሚሰጣቸው አገራዊ ጉዳዮች ቅድሚያ እንዲሰጥ አጥብቀን ለማሳሰብና ተግባራዊ እርምጃዎች መወሰድ እንዳለባቸው ለመግለጽ ነው። በኢሕአፓ በኩል የመፍትሔ ሃሳቦች የምንላቸውን እናቀርባለን።

አፄ ምንሊክ የኢትዮጵያን ሕዝብ አስተባብረው ጠላትን አድዋ ላይ ድል እንደመቱት ሁሉ መንግሥትም አገራችን ላይ አሁን እያንዣበበ ያለውን አደጋ ከፍተኛ ግምት በመስጠት አገራችንን እንድንታደጋት ሀገራዊ ጥሪ ማቅረብ ይኖርበታል። በመቀጠልም:-

1. ከተፎካካሪ ፓርቲዎች ጋር በመምከር በአገራችን ላይ የሚያንዣብበው አደጋ ለመመከት ሕዝብ በጋራ እንዲቆም ጥሪ ማድረግና አንድ አካል መሥርቶ ቀጣይ ተግባራትን አቅዶ እንቅስቃሴ መጀመር፣
2. በአገራችን ላይ የኤኮኖሚ ማዕቀብ ሊጫን እንደሚችል በመገመት መንግሥት የዲፕሎማሲ ልምድ ያላቸውን ኢትዮጵያውያን ዲፕሎማቶችን በውጭ አገራት በማሰማራት ጠንካራ የዲፕሎማሲ ሥራዎችን መሥራት፣ አገራችን ከሌሎች አገሮች ጋር ያላትን ግንኙነት በማጠናከር የማዕቀቡን ጉዳት ለመቋቋም እንዲቻል ዝግጅት ማድረግ፣
3. አባይን በተመለከተ አሁን ከሚደረገው የሦስትዮሽ ውይይት ጎን ለጎን በሌሎች የተፋሰሱ አገሮች ላይ ከፍተኛ የዲፕሎማሲ ሥራ በመሥራት በጉዳዩ ተሳትፊ እንዲሆኑ ማድረግ፣
4. ስድስተኛው ሀገራዊ ምርጫ ነፃና ርቱዓዊ እንዲሆን ከልብ መሥራት፤ የክልል መሪዎችና በየቦታው ያሉ ካድሬዎች ከምርጫ ቦርድ ጋር እንዲተባበሩ ጠንካራ መመሪያ መስጠት፣
5. ከምርጫው በኋላ ህገ መንግሥቱን ለመቀየር ወይም መሠረታዊ የማሻሻል ሥራ ተግባራዊ እንዲሆን ማደረግ፣
6. ብሄራዊ መግባባትና አገራዊ እርቅ እውን እንዲሆን ጠንክሮ መሥራት፣ ለዚህም አስፈላጊ የሆኑትን ሕጋዊ፣ ተቋማዊና ሌሎችንም አስፈላጊ ጉዳዮች በአስቸኳይ ማሟላት፣ ገና ከመነሻውም ሁሉንም ባለድርሻዎች ሙሉ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ማደረግ፣ የሚሉት ጥቂቶቹ ናቸው።

ኢሕአፓ ከመንግሥት ጋር ያለው የፖለቲካ ልዩነት እንዳለ ሆኖ የአገራችንና የሕዝባችንን ብሔራዊ ጥቅምና ክብር የሚነካ የውጭ ኃይል እጁን እያስገባ ባለበት በአሁኑ ወቅት የኢትዮጳያን ጥቅም ከሚያስቀድሙ ደርጅቶች ጎን በመቆም የውጭ ጠላትን ሁለንተናዊ ተጽእኖ ለማክሸፍ የሚታገል መሆኑን በከፍተኛ ሀገራዊ ፍቅር ያረጋግጣል።

በዚህ አኳያ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ የነበሩት ጋናዊው ኮፊ አናን የተናገሩትን ለመጥቀስ እንወዳለን። **"More than ever before in human history, we share common destiny. We can master it only if we face it together".** በግርድፉ ሲተረጎም **"በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ከምንጊዜውም በላይ የጋራ ግብን እንጋራለን፣ ግባችንን እውን የምናደርገው ግን በጋራ ስንጋፈጠው ብቻ ነው"**

ስለዚህ የኢትዮጵያ ጉዳይ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ሁሉ ከአገራችንና ከሕዝባችን ጎን መቆም ታሪካዊ ግዴታ መሆኑን ተረድተን ብሔራዊ ክብራችን ለማስጠበቅ በአንድነት እንቁም!

በአንድነት ከቆምን ምንም ኃይል ኢትዮጵያን ሊደፍር አይችልም!